# የኤሌክትሪፊኬሽን እና የሃይል ቁጠባ ግራንት ለ ሁሉም

**አላማ**
የ Takoma Park Electrification and Energy Efficiency ግራንቶች (EEE ግራንቶች) በዙርያዎ ያለውን አካባቢያዊ ዘላቂነት እና የሃይል ቁጠባ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ይረዳዎታል። እንደዚህ ዓይነት ፕሮጀክቶች የመገልገያ አጠቃቀምን ለማስተዳደር እና ወጪን ለመቀነስ፣ ቁጠባን ለማሻሻል፣ የቤት ውስጥ የአየር ጥራትን ለማሻሻል፣ ብክነትን ለመቀነስ፣ የአካባቢዎን ምቾት እና አሰራር ለማሻሻል እና ከተማው የአየር ንብረት እና ዘላቂነት ግቦች ላይ እንዲደርስ ለማገዝ ይረዳሉ። ይህ መልሰው ሊከፍሉት የሚገባ ብድር ሳይሆን፣ ስጦታ ነው።

**ማን ማመልከት ይችላል**

1. **ባለ ብዙ ቤተሰብ ህንጻ ባለቤቶች እና የንብረት አስተዳዳሪዎች፣** ባለ 4 እና ከዛ በላይ ክፍል ህንጻዎች ያላቸው።
    a. በማመልከቻዎ ውስጥ ሊገልጽዋቸው የሚችሉ ልዩ ሁኔታዎች ከሌልዎት ከ2-3 ያነሱ ክፍሎች ያሉዋቸው ህንጻዎች እንደ አንድ ቤተሰብ ቤት ማመልከት አለባቸው።
2. የመጋዘን-ግጽ ወይም የቢሮ ቦታ ያላቸው በከተዋው ውስጥ የሚገኙ **አነስተኛ ንግዶች** (እንድ ምግብ ቤቶች፣ ችርቻሮ ሱቆች፣ ሙያዊ አገልግሎት መስጫዎች፣ ቢሮዎች፣ እና የህጻናት መዋያ ማዕከላት) እና የንግድ ንብረት ባለቤቶች ለማመልከት ብቁ ናቸው።
    a. የቤት-ውስጥ-ስራ ቢሮዎች እና በቤት ውስጥ የተመሰረቱ ንግዶች ለቤት ባለቤትነት ግራንት ብቻ ለማመልከት ብቁ ናቸው።
3. **የቤት ባለቤቶች፣** የኮንዶ ባለቤቶችን እና የአከራይ ፍቃድ ያላቸውን ተከራዮች ይጨምራል።

**<u>የማመልከቻዎቹ የመጀመሪያ ግምገማ በዲሴምበር 8፣ 2021 ይካሄዳል። ከዚህ ቀን በኋላ የምንቀበለው ማንኛውም ማመልከቻ እንደ ገንዘብ አቅማችን ፍቃድ ታይቶ ይወሰናል።</u>**

እባክዎ ማመልከቻዎችን በኢሜይል ወደ GinaM@TakomaParkMD.govይላኩ። ኢሜይል መጠቀም የማይችሉ ከሆነ፣ በፖስታ ወይም ወደዚህ አድራሻ ይላኩ:

City of Takoma Park Public Works
Attn: Sustainability Manager, Gina Mathias 31
Oswego Drive
Silver Spring, MD 20910

**ከአንድ በላይ ፕሮጀክት ለምልከታ ማስገባት ከፈለጉ፣ በሚከተለው መንገድ ማመልከቻውን ይሙሉ:**

1. **ለእያንዳንዱ** ፕሮጀክት ማመልከቻ ይሙሉ።
2. አንድ ፕሮጀክት ብቻ ሊሰጥዎ በሚችልበት ሁኔታ ላቀረብዋቸው ፕሮጀክቶች በምርጫዎ መሰረት ደረጃ የሚሰጥ ተጨማሪ ደብደቤ ያቅርቡ።

    የተነጣጠሉ ፕሮጀክቶች የሚባሉት እነዚያ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው ሊተከሉ የሚችሉ እና አንዳቸው በሌላው ላይ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው። ለምሳሌ:- የአንድ ሙሉ ቤትን የኢንሱሌሽን እና አየር የመድፈን ስራዎች እንደ አንድ ፕሮጀክት ይቆጠራሉ ምክንያቱም ሁለቱ አብዛኛውን ጊዜ አንድ ላይ ስለሚጠናቀቁ እና እያንዳንዳቸው የሌላውን ተግባር እና ውጤታማነት በእጅጉ ይጎዳሉ። ከፍተኛ ውጤታማነት ያለው የ HVAC ኤሌክትሪክ መሳሪያ እና የ EV የመኪና ቻርጅ ማድረግያ ጣብያ አንዳቸው የሌላቸውን ተግባር ወይም ውጤታማነት ስለማይነኩ እንደ የተነጣጠሉ ፕሮጀክቶች ይቆጠራሉ።

ስለ ማመልከቻው ወይም ስለ ዘላቂት ግራንቱ ፕሮግራም ያልዎት ጥያቄዎች ወደ ሊመራ ይችላል:- Gina Mathias, Sustainability Manager GinaM@TakomaParkMD.gov, 301-891-7623

**የግራንቱ ዝርዝሮች**

**ግራንቶች ሽልማቶች በዓይነት**

1. **ባለ ብዙ ቤተሰብ ህንጻዎች** – እስከ 30,000 ዶላር በፕሮጀክት።
2. **ትንንሽ ንግዶች** – እስከ 30,000 ዶላር በፕሮጀክት።
3. **የቤት ባለቤቶች** – ከ5,000 ዶላር እስከ 15,000 ዶላር በቤት፣ በቤተሰብ ገቢ ላይ በመመስረት።
   a. ደረጃ 1 ገቢ የቤት ባለቤቶች እስከ 15,000 ዶላር ስጦታ ድረስ ማመልከት ይችላሉ። ግራንቱ ከፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪ እስከ 100%ድረስ ሊሸፍን ይችላል።
   b. ደረጃ 2 ገቢ የቤት ባለቤቶች እስከ 10,000 ዶላር ስጦታ ድረስ ማመልከት ይችላሉ። ግራንቱ ከፕሮጀክት አጠቃላይ ወጪው ከ50% በላይ ሊያልፍ አይችልም።
   c. ከአካባቢው መካከለኛ ገቢ በላይ የሚያገኝ ማንኛውም ሰው፣ ወይም ገቢን ላለመግለጽ አፈልጋልሁ፣ እስከ 5,000 ዶላር ስጦታ ድረስ ማመልከት ይችላል። ግራንቱ ከፕሮጀክት አጠቃላይ ወጪው ከ25% በላይ ሊያልፍ አይችልም።

| **የቤተሰብ መጠን** | ደረጃ 1 የገቢ ገደቦች (እስከ 85% አካባቢ መካከለኛ) | ደረጃ 2 የገቢ ገደቦች (እስከ 100% አካባቢ መካከለኛ) |
|---|---|---|
| 1 | 59,234 ዶላር | 69,688 ዶላር |
| 2 | 67,681 ዶላር | 79,625 ዶላር |
| 3 | 76,128 ዶላር | 89,563 ዶላር |
| 4 | 84,575 ዶላር | 99,500 ዶላር |
| 5 | 91,375 ዶላር | 107,500 ዶላር |
| 6 | 98,122 ዶላር | 115,438 ዶላር |
| 7 | 104,922 ዶላር | 123,438 ዶላር |
| 8 | 111,669 ዶላር | 131,375 ዶላር |

**የገንዘብ ድጋፍ ገደቦች**

የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው ሁሉም ፕሮጀክቶች እስከ ጁን 1፣ 2022 ድረስ መጠናቀቅ አለባቸው። አመልካቾች በ 12-ወራት ጊዜያት ውስጥ በሁለት የግራንት ሽልማቶች ተገድበዋል።

**ክፍያ እና ማመልከቻ**

የተመረጡ ባለስጦታዎች ደረሰኝ እና የፕሮጀክት መጠናቀቅ ማስረጃ ካስገቡ በኋላ በቀጥታ እንዲከፈላቸው መምረጥ ይችላሉ፣ ወይም ባለስጦታዎች ከተማው እነሱ ለመረጡት ተቋራጭ እንዲከፍልላቸው መምረጥ ይችላሉ። ግራንቱ በቅርቡ ለተጠናቀቁ ፕሮጀችቶች ተግባራዊ አይሆንም፣ ለ አዲስ ፕሮጀክቶች ብቻ ነው። ሁሉም ባለስጦታዎች የኢነርጂስታር ፖርፎሊዮ ማናጀርን በመጠቀም መመዘን እና የሃይል አጠቃቀማቸውን መዘገብ ወይም የግራንቱን ተጽዕኖ ለመመዘን ሌላ ዓይነት መለኪያ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።

**ለሁሉም ብቁ የሆኑ ፕሮጀክቶች**

ግራንቱ የሃይል ቁጠባን በሚያሻሽሉ ፕሮጀክቶች እና ከቅሪተ አካል ነዳጆች ለመራቅ የሚደረገውን ሽግግር ለማገዝ ልንጠቀምበት እንችላለን። ተመራጭ ፕሮጀክቶች በመቀጠል ያሉትን ያጠቃልላሉ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይገደቡም:

- የኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጅርክቶች
  - የተፈጥሮ ጋዝን መተካት፣ ፕሮፔን፣ ወይም የዘይት እቃዎችን ማሞቅ እና በኤሌክትሪክ ወይም በቅሪተ-አካል ነዳጅ ላይ ያልተመሰረቱ መገልገያ አማራጮች። እነዚህ ከፍተኛ ውጤታማ የኢነርጂስታር ምስክር ወረቀት ያላቸው ማሞቅያ እና ማቀዝቀዣ (HVAC)፣ የውሃ ማምሪቅያ ፓምፖች፣ የኤሌክትሪክ ማድረቅያዎች፣ የኢንዳክሽን እና የኤሌክትሪክ ማብሰያዎች፣ የኤሌክትሪክ ኮንቬክሽን አቨኖችን ያካትታል። የገንዘብ ወይም አቅርቦት የማግኘት ችግር እስካላጋጠምዎ ድረስ የምስክር ወረቀት ያላቸው የኢነርጂስታር አማራጮች አስፈላጊ ናቸው። በማመልከቻዎ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ምክንያት ያስገቡ።
  - የኤሌክትሪፊኬሽን ወጪዎች የፓኔል እና የገመድ ስራዎችን እንደአስፈላጊነታቸው ሊያካትት ይችላል። ራሳቸውን-የቻሉ የኤሌክትሪክ እድሳቶች ወይም ገመድ እንደገና የማደስ ስራዎች የኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮጀክቱ አካል ስላልሆኑ አይካተቱም።
- ሃይል ቆጣቢነትን በሚጨምረው የህንጻው ሽፍን ቦታ ማሻሻያዎች እንደ ኢንሱሌሽን፣ የአየር ቀዳዳዎችን መድፈን፣ እና የተበላሹ መስኮቶችን መቀየርን ያካትታል።

**ተጨማሪ ባለብዙ ቤተሰብ እና ንግድ ከፍት ፕሮጀክቶች**

- ለባለብዙ ቤተሰብ ህንጻዎች እና ንግዶች የተሸፈነ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የብስክሌት ማቆምያ እና ማስቀመጫ።
- ከከፍተኛ ውጤታማነት ጋር የኢነርጂስታር የምስክረ ወረቀት ያላቸው አማራጭ ተቀያሪ እቃዎች የአየር ማቅዝቀዣዎችን፣ ማሞቅያ ፓምፖችን፣ የኤሌክትሪክ ውሃ ማሞቅያዎችን፣ ፍሪጆችን፣ ልብስ ማጠብያዎችን፣ LED መብራቶችን ጨምሮ።

- የጸሃይ ሃይል ማጠራቀምያ ሰሃኖች
- የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ቻርጅ ማድረግያ መሳርያዎች

**ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ገቢ ላላቸው የቤት ባለቤቶች ተጨማሪ ብቁ ፕሮጀክቶች።***

- ከከፍተኛ ውጤታማነት ጋር የኢነርጂስታር የምስክረ ወረቀት ያላቸው አማራጭ ተቀያሪ እቃዎች የአየር ማቅዝቀዣዎችን፣ ማሞቅያ ፓምፖችን፣ የኤሌክትሪክ ውሃ ማሞቅያዎችን፣ ፍሪጆችን፣ ልብስ ማጠብያዎችን፣ LED መብራቶችን ጨምሮ።
- የጸሃይ ሃይል ማጠራቀምያ ሰሃኖች
- የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ቻርጅ ማድረግያ መሳርያዎች
- *ብቁ ለመሆን ባለቤቱ በ LMI የአየር ንብረት ሁኔታዎች ግራንት ያለፈ ጊዜ ወይም የአሁኑ ጊዜ ተሳታፊ መሆን አለበት። (https://www.edge-gogreen.com/grants/<1 ን ይመልከቱ)

**ብቁ ያልሆኑ ፕሮጀክቶች እና ወጪዎች**

- ማንኛውም የቅሪተ አካላት ነዳጆችን የሚጠቀም መሳሪያ ወይም መገልገያ።
- የኤሌክትሪክ መኪናዎች (ለ EV ዎች ነባር ማበረታቻዎችን እዚህ ይመልከቱ: https://mde.maryland.gov/programs/air/mobilesources/pages/zev.aspx)
- የዝናብ መናፈሻዎች፣ የተለያዩ የአበባ ዱቄቶች ያሉበት መናፈሻ፣ የዝናብ በርሜሎች፣ የመሬት ገጽታ ስራዎች፣ የማዳበሪያ ማጠራቀሚያዎች፣ ሊበላሹ የሚችሉ መንገዶችን የመጥረግ ፕሮጀክቶች እና ዛፍ ተከላ።
- አነስተኛ መገልገያዎች እንደ ማይክሮዌቮች፣ ቫኪዩሞች፣ ፕሪንተሮች፣ የጉልበት መሳሪያዎች፣ የሳር መንከባከብያ መሳርያዎች፣ እና የቡና መስርያዎች።
- የቤት ማስተካከያ እና ጥገና እንደ ቀለም መቀባት፣ ሬዶን፣ ሊድ፣ ሻጋታ እና የአስቤስቶስ ማስተካከያ፤ የጣርያ ስራዎች፤ ጎን መከልያዎች፤ ወዘተ... ያሉ።
- የደምወዝ እና የስራ ማስኬጃ ወጪዎች።

**አስፈላጊ - አረንጓዴ ሃይል**

ግራንት ተሸላሚዎች ከግራንት ሽልማታቸው በኋላ ቢያንስ ለ 24 ወራት የሚቆይ 100% አረንጓዴ ኤሌክትሪክ መግዛት አለባቸው። ከፔፕኮ የዋጋ ደረጃ ጋር የሚወዳደር ዋጋ ማግኘት ካልተቻለ፣ ልዩነቱን ለማካካስ በግራንት ድጋፉ ላይ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ሊጨመር ይችላል። ግራንት ተሸላሚዎች የግራንት ክፍያ ከመከፈላቸው በፊት የአረንጓዴ ሃይል ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። https://www.mdelectricchoice.com/

**አስፈላጊ - ማበረታቻዎችን ማከማቸት**

ሁሉም ተሸላሚዎች ከTakoma Park የግራንት ሽልማት ክፍያቸውን ከመቀበላቸው በፊት ተግባራዊ በሚደረጉ ግራንቶች እና ቅናሾች ሁሉ ማመልከት ይጠበቅባቸዋል። Takoma Park አሉታዊ የፕሮጀክት ወጪ የሚያስከትሉ ሽልማቶችን አያድርግም። ለምሳሌ፣ የ LED የመኪና ማቆምያ ቦታ መብራት ፕሮጀክት ለፔፕኮ ሬትሮፊት የመብራት ማበረታቻዎች ማመልከት አለበት። እባክዎን ከታች ይመልከቱ ለዝርዝር
ግብዓቶች:

የንግድ እና ባለ ብዙ ቤተሰብ ማበረታቻዎች:

1. https://homeenergysavings.pepco.com/business/overview
2. https://energy.maryland.gov/business/Pages/incentives.aspx

የቤትባለቤቶች:

1. https://montgomeryenergyconnection.org/lower-my-bill/
2. https://www.pepco.com/WaysToSave/ForYourHome/Pages/Maryland.aspx
3. https://dhcd.maryland.gov/Residents/Pages/lieep/default.aspx

ተቋራጭ ለማግኘት እርዳታ ካስፈለግዎት፣ እባክዎ የ Montgomery County ግሪን ባንክን የንግድ እና መኖርያ ዝርዝር ይመልከቱ
ተቋራጮች: https://mcgreenbank.org/partners/contractor-partners/

# የኤሌክትሪፊኬሽን እና የሃይልቁጠባ ግራንት ለ ሁሉም

እባክዎ ማመልከቻውን ሙሉ በሙሉ ያንብቡ እና ሁሉንም ክፍሎች ይሙሉ። የማመልከቻዎች የመጀመሪያ ግምገማ በዲሴምበር 8፣ 2021 ይካሄዳል። እባክዎ ማመልከቻዎን በኢሜይል ወደ GinaM@TakomaParkMD.gov ይላኩ። ኢሜል መጠቀም ካልቻሉ፣ በፖስታ ወይም ወደ እዚህ ይላኩ፡- City of Takoma Park Public Works

Attn: Sustainability Manager, Gina Mathias

31 Oswego Drive

Silver Spring, MD 20910

እባክዎ ለተጨማሪ መረጃ ሙሉ የግራንት መመሪያዎችን ይመልከቱ።

የጠያቂ ስም ____________________

የባለቤት ስም ____________________

የጠያቂ ኢሜይል ____________________

የማመልከቻ አይነት
- ☐ ባለ አንድ የቤተሰብ መኖርያ / የኮንዶ
- ☐ ባለ ብዙ ቤተሰብ ህንጻ ባለቤት / የንግድ ሀላፊ
- ☐ ክፍል ተከራይ
- ☐

የስልክ ቁጥር ____________________

አድራሻ ____________________

____________________

እባክዎ ፕሮጀክትዎን ያብራሩ። መግለጫዎ ላቀረቡት ፕሮጀክት አካል በመሆን የሚተከሉ የእያንዳንዱ እርምጃዎችን ዝርዝሮች ማካተት አለበት። እነዚህን መለኪያዎች እንደ አስፈላጊነቱ በመጠቀም የፕሮጀክት(ቶች)ዎን ተጠባቂ ዓመታዊ ጥቅሞች ግምት ያካትቱ: ዓመታዊ የሃይል ማጠን ወይም ነዳጅ ፍጆታ ቅነሳ (kWh, MMBTU, ወይም ጋሎኖች)፤ ዓመታዊ ማመንጨት (kWh አመንጭተዋል)። አስፈላጊ ከሆነ፣ የእርስዎን የሂሳብ ስሌቶች እና ግምቶች የሚያሳዩ ሰነዶችን ማያያዝ ይችላሉ።

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

የሃይል ኦዲት አድርገዋል? አዎ ከሆነ፣ መቼ፣ እና ይህንን ፕሮፖዛል ለማዘጋጀት ረድቶታል?

____________________

የፕሮጀክቱን እያንዳንዱን ክፍል እስከ ዋጋው በመግለጽ የሚከተለውን ሰንጠረዥ ይሙሉ። እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ረድፎችን መጨመር ይችላሉ። የግምቱን ምንጭ ይዘርዝሩ (የአቅራቢ ግምት፣ ጨረታ፣ የቤት ክምችት የመስመር ላይ ዋጋ፣ ድረ-ገጽ፣ ወዘተ...)። የሚገኝ ከሆነ፣ የዋጋ ግምት ሰነድ እንደ ተያያዥ ያቅርቡ። ወጪዎች ሁለቱንም የቁሳቁስ እና የጉልበትን ማካተት አለባቸው። ይህ መረጃ የማመልከቻዎን ደረጃ ለመስጠት ወሳኝ ነው። ጥሬ ግምቶች ተቀባይነት አላቸው፣ በተለይ ዝርዝር ምርመራ ለሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች፣ በርካታ ጨረታዎችን ለማስተባበር ካስፈለግዎት፣ ወይም አንድ ፕሮጀክት ተለዋዋጭ ወጪዎች ካሉት።

| የመስመር ንጥል: (የመሳርያ አይነት፣ የጉልበት ስራ፣ አስተዳደር፣ ወዘተ...) | የግምት ምንጭ | ወጪ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| **የፕሮጀክት አጠቃላይ ወጪ:** | **የተጠየቀው አጠቃላይ የግራንት መጠን*:** | ***እባክዎ ለግራንት ሽልማት ደረጃዎች ገጽ 2ን ይመልከቱ** |

የገንዘብ ድጋፍ ምንጮች: ለፕሮጀክቱ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሁሉንም የገንዘብ ድጋፍ ምንጮች ይዘርዝሩ። ማመልከቻዎችን፣ የሽልማት ደብዳቤዎችን፣ ወይም ካመለከቱባቸው፣ ወይም ለማመልከት ካቀዱባቸው የአገልግሎት እና ሌሎች የማበረታቻ ፕሮግራሞች ጋር የሚያያዙ ሌሎች ሰነዶችን ያያይዙ።

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

የፕሮጀክት የጊዜ መስመር: ያቀረቡትን የፕሮጀክት የጊዜ መስመር ይግለጹ። ሁሉንም የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ደረጃዎች እና ተጠባቂ የማጠናቀቅያ ቀኑን ይዘርዝሩ። የፕሮጀክቱ ግንባታ እና ተከላ ለTakoma Park ከተማ ከሚቀርቡ የማጠቃለያ ሪፖርቶች እና ደረሰኞች ጋር እስከ ጁን 1, 2022 ድረስ መጠናቀቅ አለበት። የፕሮጀክት የጊዜ መስመርዎን ከዚህ ጊዜ ገደብ ጋር በሚጣጣም መልኩ ያዘጋጁ፣ ተቋምዎ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የመርሃ-ግብር ማዘጋጀት ስጋቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት (ለምሳሌ:- የአገልግሎት መስጫ መርሃ ግብሮች፣ በዓላት፣ የአቅርቦት ሰንሰለት መዘግየቶች፣ የአየር ሁኔታ፣ ወዘተ...)፣ እንዲሁም የመሳርያዎች እና ቁሳቁስ መምርያ ጊዜዎች።

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

<u>ለንግድ አመልካቾች:</u>

የንግድ ስም ______________________________

የንግድ አይነት ________________________

በንግድ ውስጥ የቆየበት አመት ________________

የሰራተኞች ብዛት በቁጥር __________________

**ከዚህ ቀደም ማንኛውንም አይነት የከተማ ስጦታ ተቀብለዋል? አዎ ከሆነ፣ መቼ እና ለምን?**

<u>ለባለ ብዙ ህንጻ ባለቤቶች እና አስተዳዳሪዎች:</u>

የህንጻው ስም ______________________________

የነዋሪዎች የህንጻው ________________________

ቁጥር አይነት ________________________

የክፍሎች ብዛት በቁጥር ________________________

**ከዚህ ቀደም ማንኛውንም አይነት የከተማ ስጦታ ተቀብለዋል? አዎ ከሆነ፣ መቼ እና ለምን?**

ለአንድ-ቤተሰብ ቤት እና ኮንዶ ክፍል ባለቤቶች:

የቤት እድሜ ____________________

በቤት ውስጥ የኖሩበት አመታት____________________

የነዋሪዎች ብዛት በቁጥር ____________________

አጠቃላይ የቤተሰብ ገቢ* ____________________

**ከዚህ ቀደም ማንኛውንም አይነት የከተማ ግራንት ወይም የዋጋ ቅናሽ ተቀብለዋል? አዎ ከሆነ፣ መቼ እና ለምን?**

*ከአጠቃላይ የፕሮጀክት ወጪው 25% የሚበልጥ እና / ወይም ከ5,000 ዶላር በላይ የግራንት መጠን የሚያመለክቱ ከሆነ፣ ለሁሉም ገቢ የሚያስገኙ የቤተሰብ አባላት ከቅርብ ጊዜ የፌደራል ገቢ ግብር ተመላሽዎ ቅጽ 1040 ገጽ 1 እና ገጽ 2ን ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት። ከመጨረሻው የግብር ተመላሽዎ ጀምሮ በገቢዎ ላይ አስገራሚ ለውጥ እያጋጠምዎት ከሆነ ማብራርያ ያካትቱ።

ለሁሉም:

የስነ ህዝብ መረጃ (በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እና የተመሰገነ)

የንግድ ባለቤቱ(ዎቹ) / የቤት ባለቤቱ(ዎቹ) / ዋና አመልካቹ(ዎቹ) ዘር::

____________________

ለ እንደ ቋንቋ ትርጉም / ትርጓሜ፣ ያሉ ግንኙነቶች ማረፊያ ያስፈልግዎታል?

____________________

የንግድ ባለቤቱ(ዎቹ) / የቤት ባለቤቱ(ዎቹ) / ዋና አመልካቹ(ዎቹ) እድሜ:

____________________

**የአመልካች ፊርማ**

**ይህንን ማመልከቻ በመፈረም ሁሉም ነገር እውነት እንደሆነ እና ምንም አይነት የውሸት መረጃ ሆንብለው እንዳላቀረቡ ያረጋግጣሉ። ለዚህ ግራንት የውሸት መረጃ ማቅረብ ከTakoma Park ከተማ የሚሰጠውን ማንኛውንም እንዲሁም ሁሉንም የግራንት ሽልማቶች ማጣትን ሊያስከትል ይችላል።**
የማመልከቻዎን ማረጋገጫ በ48 የስራ ሰአታት ውስጥ ማግኘት አለብዎት። የግራንት ሽልማቶች የሚገለጹት በ
ዲሴምበር 30፣ 2021 ወይም ከዚያ ቀደም ብሎ ይሆናል።

ገጹ ለ ተጨማሪ መረጃ ባዶ ተደርጓል